# ADDA BILISUMMAA OROMOO

**OROMO LIBERATION FRONT** جبهة تحرير اورومو

Gaafa: 16/09/2017
Date: تاريخ

Lakk.: **014/stm-abo/2017**
No.: رقم

## በሐመሬሳ ላይ ለተፈጸመው የጅምላ ግድያ የወያኔ መንግስት የእጁን ያገኛል!

(በሐመሬሳ የተፈጸመውን ድርጊት በማውገዝ ከኦሮሞ ነጻነት ግንባር የተሰጠ መግለጫ)

በትላንትናው ዕለት (መስከረም 15 ቀን 2017ዓም) ከ10,000 በላይ የሚሆኑ የኦሮሞ ዜጎች በሶማሌ ክልል መንግስት “የልዩ ፖሊስ” ሃይል በመሳሪያ አፈሙዝ ማስፈራሪያ ደርሶባቸው ቤት-ንብረታቸውን ትተው በ80 ተሽከካሪዎች ተጭነው በመሰደድ በሐረር ከተመ በሚገኘው የሐመሬሳ ካምፕ ውስጥ እንዲሰፍሩ መደረጋቸው ተሰማ። እነዚህ ያለ ኣንዳች ቅድመ-ዝግጅትና ማስጠንቀቂያ ይህን በመሰለው ኣሳዛኝ ሁኔታ ኑሮኣቸው ተናግቶ በስደት ላይ ያሉ የኦሮሞ ዜጎች ዛሬ ጠዋት (መስከረም 16 ቀን 2017ዓም)የምግብ፣ የመጠጥ ውሃና መድሃኒት ኣገልግሎት እንዲሰጣቸው መንግስትን በጠየቁበት ወቅት ኣንዳችም  ሰብዓዊ ርህራሄ የሌለውና የኦሮሞን ህዝብ እንደደመኛ ጠላቱ የሚቆጥረው የወያኔ መንግስት ጥይት ኣርከፍክፎባቸው ከ10 በላይ ሰዎችን ሲገድል ቁጥራቸው ለጊዜው በውል ያልታወቀ ዜጎችን ደግሞ ኣቆሰለ።

በዚህ ሁኔታ በስደት ላይ ላሉ ሰዎች ምግብና ውሃ፣ እንዲሁም መድሃኒት፣ ኣልባሳትና ሌሎችንምም ለኑሮ ኣስፈላጊ በሆኑ ኣገልግሎቶች ሲደረስላቸው ሲገባ በተቃራኒው የወያኔ መንግስት በዜጎቻችን ላይ የፈጸመው የጅምላ ግድያ መሆኑን የኦሮሞ ነጻነት ግንባር በጥልቅ ሃዘንና ከፍተኛ ቁጣ እየገለጸ፥ ይህ የወያኔ ድርጊት በሁሉም ሰብዓዊ ፍጡር ሊወገዝ የሚገባው መሆኑንም ኣጥብቆ ያስገነዝባል።

ወያኔ ዛሬ ይህን መሰሉን ዘግናኝ እርምጃ በህዝባችን ላይ በወሰደበት በዚህ ቦታ (ሐመሬሳ) ላይ ከሁን ቀደምም በመቶዎች የሚቆጠሩ የኦሮሞ ተወላጆችን ያለ ኣንዳች ጥፋት በእስር ቤት በማጎር ምግብ፣ ወሃና የህክምና ኣገልግሎች በመንፈግ በረሃብና በበሽታ ተሰቃይተው እንዲያልቁ ማድረጉ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው። በወያኔ መንግስት በህዝባችን ላይ ሲፈጽም በነበረውና ኣሁንም እየተፈጸመ ባለው በዚህ ወደር የማይገኝለት የዘር-ማጥፋት ተግባር ህዝባችን በሃገሩ ላይ እንደኣውሬ ታድኖ መገደልና ለከፋ ጭቆና መዳረጉ የሚገታው ህዝባችን የጭቆና (የባርነት) ኣገዛዝ ስርዓትን ከላዩ ላይ ኣሽቀንጥሮ በመጣል ነጻነቱን በመጎናጸፍ እራሱ ባቋቋመው ሉዓላዊ መንግስት ስር መተዳደር ስችል ብቻ መሆኑ የኦነግ ጽኑ እምነት ነው።

ስለሆነም በሁሉም ቦታ የሚገኙ የኦነግ መዋቅሮች፣ በሁሉም ኣውደ-ግንባሮች የሚገኘው የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት፣ እንዲሁም ባጠቃላይ በሃገር ቤትና በውጪ ሃገራት ያለው መላው የኦሮሞ ህዝብ ከጠንካራ የኦሮሞ ብሄራዊ ስሜት በመነጨ ኣንድነትና ጀግንነት በጋራ ተነስተን ጠላታችን ከምድረ-ገጽ ሊያጠፋን ኣቅደዉ እየተገበረው ያለውን ይህን እቅድ ለማክሸፍ፥ ይህን ላለፉት 26 ዓመታት የኦሮሞን ህዝብ  ደመኛ ጠላቱ ኣድርጎ በመፈረጅ እየፈጀው ያለውን መንግስት በመጣል ሰላምና ነጻነታችንን ኣውን ኣድርገን ለዛሬው ህይወታችንና ለልጆቻችን መጻዒ ሕይወት ዋስትና ለማስገኘት እንንቀሳቀስ!

በሁሉም መልኩ በህዝባችን ላይ ሲፈጽም ለነበረውና እየተፈጸመ ላለው ግድያና ሰቆቃ ሁሉ ወያኔ የእጁን የሚያገኝበት ቀን ሩቅ ኣይሆንም!

**ዘመኑ የጭቆና ፍጻሜ ዘመን ነው !**

**ድል ለኦሮሞ ህዝብ !**

**የኦሮሞ ነጻነት ግንባር**
**መስከረም 16 ቀን 2017ዓም**

P.O.Box 6973 Asmara, Eritrea   Tel: 2911110236,  Email: Caalchis@gmail.com, www.oromoliberationfront.org